# “ከማሳ እስከ ጉርሻ”

## በይበልጣል መኮንን

ግብርና ሲወሳ የምግብ ጥያቄ ጉዳይ ቀድሞ የሚታወስ ቢሆንም ክፍለ ኢኮኖሚውን በማሳደግ ለድህነት ቅነሳ ያለው ፋይዳ ከሚጠበቀው በላይ ነው። ግብርና በአብዛኛው የዓለም ሀገራት የጀረባ አጥንት ሲሆን ለኢኮኖሚያቸው ማደግ የነበረው ጠቀሜታም ቢሆን እንደ ማዕዘን ድንጋይ ሆኖ አገልግሏል።

እንደሌሎች ሀገሮች ሁሉ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ምርኩዙም ሆነ መነሻው ይኸው የግብርናው ዘርፍ ነው። ከዚህ ጋር ተያይዞም አብዛኛው የኢትዮጵያ ህዝብ በግብርና ስራ ላይ እንደተሰማራ ይታወቃል። የኢትዮጵያ ግብርና በአብዛኛው ዝናብ መሰረት ያደረገና ኋላቀር በሆነ የእርሻ ስርዓት በተከተለ ግብርና የሚተዳደር ነው። በዚህም የተነሳ ምርትና ምርታማነት በእጅጉ ዝቅተኛ በመሆኑ አብዛኛው ህዝብ በድህነት ወለል ውስጥ እንዲኖር አስችሎታል።

አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ኢትዮጵያ ለግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ ሊውል የሚችል የለማ መሬት ፣ ከፍተኛውሃ ፣ ሁሉንም አይነት የአየር ንብረት ያካተተ እና ሰፊ የሰው ኃይል እንዳላት ግልፅ ነው። ዘርፉን ለመምራት የሚያስችል ከፍተኛ በጀት ተመድቦለት ወደ ስራ ከተገባ በርካታ ዘመናት ተቆጥረዋል።

ይሁን እንጅ ይህ ብዙ የሰው ኃይል የተሰማራበት እና ከፍተኛ በጀት የተመደበበት የግብርናው ዘርፉ በሚፈለገው ልክ የማህበረሰቡን ፍጆታ በበቂ ሁኔታ እየሸፈነ አይደለም። እንደሚባለውም ኢኮኖሚውን ደግፎ የምግብ ዋስትናን በማረጋገጥ በኩል ያለው ውጤታማነትም ብዙ የተደከመለትን ያክል እንዳልሆነ የአደባባይ ሚስጥር ነው። ለዚህም በዋናነት አርሶ አደሩ ከመኸር ጥገኝነት ካለመላቀቁም በተጨማሪ ዘመናዊ የእርሻ አሰራሮችን ተደግፎ አለመመራቱ እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች እንደ ችግር ተደርገው ይነሱበታል።

ችግሮች በየትኛውም ጊዜ መግጠማቸው አይቀርም ሆኖም ለችግሮች ቀድሞ የመፍትሄ ሀሳቦችን ማመቻቸት ተገቢ ነው። ከዚሁ ጉዳይ ጋር ተያይዞ በስፋት የሚነሳው የግባት አቅርቦት ችግር በተለይም የአፈር ማዳበሪያ እጥረት ፣ የስርጭት መጓደል የምርት ዘር እጥረት እና የህገ ወጥ የአፈር ማዳበሪያ ዝውውር በእጅጉ መገታት ያለበት ሲሆን መንግስትም ቢሆን በዚሁ ጉዳይ አብክሮ በመስራት ችግሩን ዘላቂ በሆነ መንገድ ለመስራት አልሞ መንቀሳቀስ ይኖርበታል።

መንግስት የኩታ-ገጠም አስተራረስ ዘዴን ማስፋት ፣ የቴክኖሎጅ ግባቶችን ለአርሶ አደሩ ተደራሽ ማድረግ ፣ ቴክኖሎጅውን በማዘመን በኩል አጠናክሮ መስራት ፣ ሁሉም ሰው ለጥቅምና ለግዴታ ተገዥ እንዲሆን የህግ ድንጋጌ በማስቀመጥ የኩታ ገጠም እርሻ አተገባበርን በሕጋዊ ማዕቀፍ የተካተተ ማድረግ ፣ አርሶ አደሮች ገበያውን በቀላሉ በጋራ እንዲቆጣጠሩ የገበያ ትስስር በመፍጠር እረገድ መንግስት አርሶ-አደሮች የኩታ-ገጠም አስተራረስ ዘዴን ተጠቅመው ምርትና ምርታማነትን እንዲያሳድጉ ድጋፍና ክትትል ስራውን አጠናክሮ መስራት ይኖርበታል።

ሌላው ጉዳይ አርሶአደሩ ከማሳ ዝግጅቱ ጀምሮ በቡቃያው እንዲሁም በእሸቱ ሰብሎችን እንዲጠብቅ ፣ ማሳውን እንዲፈትሽ እና ክትትል እንዲያደርግ የሚደረገውን ተግባር አጠናቅሮ

ማስቀጠል ያስፈልጋል፡፡ አርሶአደሮች ከግብርና ምርምር ተቋማት ጋር ያለቸውን ግንኙነት በማሳደግ ምርትና ምርታማነት ለድህነት ቅነሳው ያለውን ፋይዳ በተግባር ማሳየት ተገቢ ነው፡፡

የምርት አቅርቦትና ፍላጎት ሚዛንን ለመጠበቅ እብረተሰቡ የተረጋጋ ኑሮ እንዲኖር በማድረግ በኩል ምርትና ምርታማነትን የሚጨምሩ የግብርና ምርምር ተቋማትን አቅም ማሳደግ ይገባል፡፡ ግብርና ምርትን በመጠንና በፍላጎት ልክ በማምረት ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ደግሞ ዘመናዊ እና አዳዲስ የግብርና ቴክኖሎጅዎችን ማስፋፋት እና በሙያ መደገፍ አስፈለጊም ግዴታም ነው፡፡
በአጠቃላይ የአርሶአደሩን የሰብል ልማት የሚያስጠብቁ ዘመናዊ የግብርና ቴክኖሎጅዎችን በማስታጠቅ ለመሬት የሚወጣውን ጉልበት መቀነስ እና የመሬትን ለምነት በመጠበቅና በማስጠበቅ “ከማሳ እስከ ጉርሻ” ያለውን ምርት የተትረፈረፈ እንዲሆን ለማስቻል የሁሉንም ያለሰለሰ ጥረት የሚጠይቅ ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ ምርትን በማሳደግ ጥራት ያለው ተወዳዳሪ የሆነ ምርት ማምረት እና በምግብ ራስን የመቻል ፍላጎትን ማሳካት የሁሉንም እርብርብ ይሻል ሰላም፡፡

ስም----------------------------

ፊርማ---------------------------

ቀን------------------------------